# 2 ውስጥ የኢሚግሬሽን ጠበቃ ፍለጋ ላይ

በUK

UK

በ UK ውስጥ ጥገኝነት ሲጠይቁ ማድረግ የሚችሉት ጥሩው ነገር በተቻለ ፍጥነት ጥሩ ጠበቃ ማግኘት ነው። ብዙ ጊዜ ነጻ የሕግ ባለሙያ አገልግሎት ማግኘት የምቻለው በ'legal aid' በኩል ነው። ለሁሉም ሰው በቂ ጠበቆች ስለሌሉ እና ሁሉም ጠበቆች ጥሩ ስላልሆኑ ይህ ሁልጊዜ ቀላል አይደለም::

ነፃ ጠበቃ እንዴት መፈለግ እንደሚቻል አንዳንድ ሃሳቦች ከዚህ በታች ቀርበዋል:-

ወደ **https://find-legal-advice.justice.gov.uk/**,
በመሄድ በ 'post code' ያጣሩ እና ፍለጋውን ለመገደብ “"immigration and asylum" ላይ ምልክት ያድርጉ።

ለግለሰቦች እና ቡድኖች የህግ ምክር፣ የጉዳይ ስራ እና ውክልና ለማግኘት በአቅራቢያዎ የሚገኘውን የህግ ማእከል ያግኙ
**https://www.lawcentres.org.uk/about-law-centres/law-centres-on-google-maps/geographically**

በአካባቢው የሕግ ባለሙያ ድጋፍ ወይም የስልክ ጥሪ አገልግሎት የሚሰጥ ድርጅት ይፈልጉ።
በመስመር ላይ **“asylum/migrant support”** + የከተማዎን ስም መስመር ላይ በማስገባት ይፈልጉ።

ጠበቃ ለማግኘት እንዲረዳዎት እንደ **Care4Calais (+44 7519 773268)** ያለ ድርጅት ይጠይቁ;
ድርጅቶችን ማነጋገር ጠበቃ እንደሚያገኙ ዋስትና አይሆንም።

በሚያረፉበት ሆቴል ውስጥ ጓደኞችን፣ ቤተሰብን እና ሌሎች ሰዎችን ጥሩ ጠበቃ ካላቸው ይጠይቁ::

---

**Asylum Aid** የአንድ ጊዜ ነፃ፣ ሚስጥራዊ እና ገለልተኛ የህግ ምክር በስልክ ይሰጣል:-
ሰኞ 2:00pm እስከ 4:30pm እና, ሀሙስ ከ10:00pm እስከ 12:30pm, በ **+44 2073 549264** ሊደውሉላቸው ይችላሉ።

---

**ስለ 'Legal Aid' (እንዴት ጠበቃ በነፃ ማግኘት እንደሚቻል) በRight to Remain የተዘጋጀ ማስታወሻ:-**

> የህግ እርዳታ *'Legal aid'* ምንም ወይም አነስተኛ ገቢ ያላቸውን ሰዎች የህግ ምክር እንዲያገኙ የሚያስፈልገውን ወጪ ለመሸፈን ይረዳል::
> መንግሥት ለዚህ ዓላማ ገንዘብ ይመድባል እና የሕግ እርዳታ *'legal aid'* ክፍያዎች በቀጥታ ለህጋዊ ምክር ሰጪው ወይም ጠበቃ ይከፈላሉ:: የህግ ድጋፍ ጠበቃ ለሆም ኦፊስ *'Home Office'* አይሰራም።
> አንዳንድ ጊዜ ሰዎች ለጠበቃ ክፍያ ስለማይከፍሉ፣ ይህ ማለት እንደ የግል (የተከፈለ) ጠበቃ ጥሩ እንደማይሆኑ ያስባሉ። በእኛ ልምድ፣ በጥገኝነት፣ በኢሚግሬሽን እና በሰብአዊ መብቶች ላይ የሚሰሩ አብዛኛዎቹ ምርጥ የህግ ባለሙያዎች በህግ ድጋፍ *'Legal aid'* ስር የሚሰሩ ናቸው። የሕግ ውክልና ጥራት ለህጋዊ እርዳታ *'legal aid'* ጠበቆች እና ለግል ጠበቆች ብዙ ሊለያይ ይችላል። ጠበቃዎ ጥሩ ስራ እየሰራ መሆኑን ለመከታተል እንዲችሉ የህግ ሂደቱን በተቻለ መጠን መረዳት በጣም አስፈላጊ ነው።
>
> ይህ መረጃ የተወሰደው ከ Right to Remain Toolkit/ስብስብ ነው; በUK ውስጥ ስለ ጥገኝነት ጥያቄ ሌሎች ብዙ ጠቃሚ መረጃዎችን የያዘ ድህረ ገጽ ነው። እና በተለያዩ ቋንቋዎች ይገኛል **https://righttoremain.org.uk/toolkit/** ላይ ሊያገኙት ይችላሉ::

**Note**
አንዳንድ ጊዜ ሰዎች የጥገኝነት ማመልከቻ ሂደቱን ለማፋጠን ለHome Office ደብዳቤ ለመጻፍ ከጥገኝነት ጠያቂዎች ገንዘብ ለማግኘት ይሞክራሉ። ይህ ማጭበርበር ነው እና ገንዘብዎን ለእነሱ መስጠት የለብዎትም:: 'Legal aid' ለቋንቋዎ አስተርጓሚ ገንዘብ መክፈል አለበት። ለአስተርጓሚ መክፈል ወይም የራስዎን አስተርጓሚ ማምጣት የለብዎትም። ማስታወሻ: በUK ውስጥ ጠበቃ ማግኘት በጣም ከባድ ሊሆን ይችላል። ጠበቃ ለማግኘት የሚደረግ ማንኛውም ሙከራ ማስረጃን መመዝገብ አስፈላጊ ነው፣ ለምሳሌ የዋትስአፕ መልእክቶች፣ ኢሜይሎች፣ የስልክ ጥሪዎች ወዘተ::

CHANNEL INFO PROJECT

Refugee Legal Support

**Disclaimer:**
This translation is not certified and has been produced using information from the original English and French documents.